የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰሜን ምሥራቅ የደቡብ ምሥራቅ እና
የመካከለኛው አሜሪካ የኒውዮርክ ሃገረ ስብከት
ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of New York, Northeast, Southeast and
Central United States of America

ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፳፻ወ፩ ዓ.ም

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ አሜን

“ኢትፍርሃ አንትንሰ እስመ አአምር ከመ ኢየሱስሃ ዘተሰቅለ ተኃሥሣ ። እናተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና” ማቴ፡፳፰ ፡ቊ ፭

የተከበራችሁ አባቶቼ እና እናቶቼ ወድሞቼና እኅቶቼ ከሁሉ አስቀድሞ ለፍቅሩ ወረት ለመግቦቱ ንፍገት ለጥበቃው ሀኬት የሌለበት ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን እና እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላምና በጤና አደረሳችሁ በማለት በሀገረ ስብከቱ ስም መልካም ምኞቴን ስገልጽ በታላቅ ደስታ ነው።

ብርሃነ ትንሣኤው የክርስቲያኖች ትንሣኤና ብርሃን ነው።በመሆኑም በክርስቶስ ለሚኖሩ ክርስቶስን ለሚፈልጉ ሁሉ ጨለማ ጋርዶአቸው መሰናክል ገጥሞአቸው እንዳይሰናከሉ አይዞአችሁ አትፍሩ እነሆ ተነስቶአል የሚል የምሥራች ቃል የተሰማበት ታላቅ በዓል ነው። ይህን ታላቅ በዓል ስናከብር ከነገረ መስቀሉ በመነሳት ውለታዉን እንድናስብ ይጋብዘናል። የፍቅር አባት የሰላም አምላክ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች መከራ ተቀበለ በቀራንዮ አደባባይ ያለበደሉ ከወንበዴዎች ጋር ተሰቀለ ስለሆነም በሞቱ ሞትን ድል ነሣ ሲያልንም በረበረ የታሰሩትን ፈታ ዲያብሎስን አሰረ የፍርሀትን መንፈስ ከሰው ልጆች አስወገደ ከዚህም የተነሳ ምድር በደመ ክርስቶስ ታጥባ ታላቅ በአልን አደረገች ስትል ቤተ ክርስቲያናችን በዓለ ትንሣኤውን ታከብረዋለች ”ትንሣኤከ ለእለ አመነ ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ”ትንሣኤህን ለምናምን ለእኛ ብርሃንህን ላክ በማለትም ትጸልያለች ትዘምራለች።
ቤተ ክርስቲያን የትንሣኤው ታዳሚ ለሆኑት ልጆቿ ህይወታቸው በፈቃደ እግዚአብሔር እንዲመራ ያለ ፍርሀትና ያለሰቀቀን በደስታ እንዲኖሩ ጉዞአቸውና ዓላማቸው ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንዲሆን ትመክራለች ታስተምራለች።

በመድኃኒታችን ሞት ህይወትን ያገኛችሁ ወገኖቼ

ሰወች ለሚያደርጉልን በጎ ሥራ ሁሉ እገሌማ ባለውለታየ በማለት ብዙ እንላለን በርዕግጥም ተገቢ ነው። ውለታ ቢስ መሆን አሳፋሪ ነውና፡፡ ወገኖቼ አምላካችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አልጫ ዓለም ለማጣፈጥ እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ዘመን ከውለታም በላይ ውለታ የዋለላቸው ገቢረ ተአምራት ያደረገላቸው ተቸግረው የረዳቸው ተርበው የመገባቸው ታመው የፈወሳቸው ብዙ ወገኖች ነበሩ በመከራው ቀን ግን ከብዙዎች ጥቂቶች አልነበሩም ምክንያቱም

፪

በፍርሃት መንፈስ ደንዝዘው ውለታ ለመክፈል አልታደሉምና። ይሁን እንጂ ለምስክርነት የአምላካችን ንጹሕ ፍቅር የጠራቸውና ውለታው ያስገደዳቸው እናቶቻችን ገና በጨለማው ወደመቃብሩ በመገስገሳቸው ባለውለታቸውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚፈልጉ በማረጋገጥ የእግአብሔር መልአክ “እናተስ አትፍሩ” ብሎአቸው ነበርና እነሆ በዚያው ቅጽበታዊ ሰአት ከቅዱሳን መላእክት ያዩትን እና የሰሙትን ለአባቶቻችን ለቅዱሳን ሐዋርያት ሊነግሩ ሲጓዙ የፈለጉትን ኢየሱስ ክርስቶስን አገኙት። “ደስ ይበላችሁ” የሚለውንም የደስታ ቃል ከፈለጉት የሰላም አምላክ ለመስማት ታደሉ። ወድቀውም ሰገዱለት በድጋሜም በመድኃኒታችን ቃል ‘አትፍሩ’ ተባሉ ሄደውም ወንድሞቼ ለአላቸውና ለመረጣቸው ለደቀመዛሙርቱ ገሊላ እንዲሄዱ በዚያም እንደሚያዩት እንዲነግሩአቸው አዘዛቸው። የተናቁትን እና የተዋረዱትን ከፍ ከፍ ማድረግ የቸርነቱ ሥራ ነውና።

ቤተ ክርስቲያኑ ትሆኑ ዘንድ በንጹሕ ደሙ የዋጃችሁ ወገኖቼ

እንደሚታወቀው ይህ ዓለም አስፈሪና አስቸጋሪ ነው።ስለሆነም አይዞህ አይዞሽ አዞአችሁ የሚል ለበ ሙሉ የሚያደርግ የፍርሃት መንፈስን የሚያስወግድ መንፈሳዊ ወኔ የሚሰጥ ግድ ያስፈልጋል።እንዲህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ሀብት የሚገኘው ደግሞ በገንዘብና በቁሳቁስ ብዛት አይደልም በሌላ መልኩም በዓለም ጥበብና ፈልስፍናም አይደለም።ይህም ይረጋገጥ ዘንድ ብዙዎች እያወቁ ያላወቁ እያላቸው የሌላቸው ሆነው እንደ ሰው ሰውኛው አባባል ይህ ጎደላቸው ሳይባል በፍርሃተና በጭንቀት ሲመላለሱ ይታያሉና።
በአንጻሩም ምንም ሳይኖራቸው እንደአላቸው ሆነው እግዚአብሔርን በመፍራትና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ከማንኛውም በላይ ለእኛስ እግዚአብሔር አለን በማለት በደስታ ሲሚመላለሱ ይታያሉ።
በሌላ መልኩም በተሰጣቸው ብዕልና ጸጋ ሳይመኩ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ከተሰጣቸው ለሌለው በማካፈል በሥጋ ፈቃድ ያይደለ በፈቃደ እግዚአብሔር የሚኖሩትን ስናይ ልዩነቱ ጎልቶ ይታያል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰሜን ምሥራቅ የደቡብ ምሥራቅ እና
የመካከለኛው አሜሪካ የኒውዮርክ ሃገረ ስብከት
ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of New York, Northeast, Southeast and
Central United States of America

<u>ወገኖቼ</u> ብዙ ሰዎችን የሚያስጨንቃችውና ከእግዚአብሔር የሚለያአቸው የጊዚያዊው ዓለም ሃሳብና ውጣ ውረድ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊው ያስተምሩናል ስለሆነም በእንዲህ አይነቱ ውቅት አይዞህ ባይ ያስፈልጋል፡ለምሳሌ ያህል የተወሰኑ ጥቅሶችን ከቅዱስ መጽሐፍ ብንመለከት በሠሩት ክፉ ሥራ እና በፈጸሙት በደል ጭንቀትና ፍርሃት የያዛቸውን የዮሴፍን ወንድሞች ለይቅር ባይነት ዝግጁ በሆነውና በመረጠው በወንድማቸው አማካኝነት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "ዮሴፍም አላቸው አትፍሩ እኔ በእግዚአብሔር ፈንታ ነኝን? እናተ ክፉ ነገርን

፫

አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው"ዘፍ ፶፡፲፱
ለብዙ ሕዝብ ድኅነት መሸጥ ዮሴፍ ለክርስቶስ ምሳሌው ነውና ። "ዘምስለ ዮሴፍ ተሰይጠ ከመ ይስፍር ሲሳየ ለሕዝብ" እንደተባለ። ምን እንበላለን እኛስ ልጆቻችንስ እንዴት እንኖራለን በማለት ሲጨነቁ እግዚአብሔር በዮሴፍ አድሮ "አሁንም አትፍሩ እኔ እንናተን እና ልጆቻችሁን እመግባችኋለሁ ይላል።" ዘፍ ፶፡፳፩
ስጦታው የማያልቅበት ልዑል አምላክ እንዴት እንደሚሰጥ ሲአስተምርም "ሰላም ለእናተ ይሁን አትፍሩ አምላካችሁና የአባታችሁ አምላክ በአይበታችሁ የተሰወረ ገንዘብ ሰጣችሁ ይላል።ዘፍ ፵፫ ፡፳፫።
የመከራ ቀንበር የትሸከሙትን በጠላት የተከበቡትንም እግዚአብሔር በወዳጁ በሙሴ አድሮ "ለሕዝቡ አትፍሩ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብጻውያን ለዘለዓለም አታዩአቸውምና ቁሙ ዛሬ ለእናተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ እግዚአብሔር ስለእናተ ይዋጋል።እናንተ ዝም ትላላችሁ" ዘጸ፲፬፡፲፫።
በወሬ የሚፈቱትን በማየት የሚደነግጡትን ብቸኝነት የሚሰማቸውንም "ጽኑ አይዞአችሁ አትፍሩ ከፊታቸውም አትደንግጡ አምላክህ እግዚአብሔር እርሱ ከአንተ ጋር ይሄዳል፡አይጥልህም አይተውህም"ዘዳ፴፩ ፮።ይላል።

<u>እግዚአብሔር የመረጣችሁና የአከበራችሁ ሁሉ</u>

ከላይ እንደሰማነው እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ትምህርት ክርስቲያናዊ ግዴታችንን ለመወጣት እርስ በእርስ በመደጋገፍ ሕገ እግዚአብሔርን እንጠብቅ በልዩ ልዩ ችግር የሚገኙ ወገኖቻችንንም በቃል ያይደለ በተግባር አይዞአችሁ አትፍሩ እንበላቸው በችግራቸውም እንርዳቸው። ቤተ ክርስቲያንም የልጆቿን አልኝታነት ትፈልጋለችና ልጆችሽ አንድ ሆነን ከፊትሽ ቆመናል የእናትነት ፍቅርሽ አይለየን እንበላት።በአንጻሩም ርኩስ መንፈስን ከአንተ ጋር ዝምድና የለንም የአንተ ሥራ መለያየት ጥላቻ ውዝግብ ነውና በቃ እንበልው። እንደ ክርስትና ምግባር በችግራችንም ሁሉ ሊያደርጉልን ወደማይችሉ ሰዎች ከመጮኽ፤ ወደ እግዚአብሔር እንጨኽ፡ ጩኽታችን ልባዊ እና እውነተኛ ጩኽት እስከ ሆነ ድረስ መልስ ለማግኘታችን ጥርጥር የለበትምና። በቸርነቱ ብዛት ከምናውቀውም ከማናውቀውም ነገር ጠብቆ ለብርሃነ ትንሳኤው የአደረሰን አምላክ የተመሰገነ ይሁን። በድጋሜ እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው አደረሳችሁ።

አባ አብርሃም
የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ